# አድርገህልኛልና

አድርገህልኛልና በቸርነትህ አመሰግንሃሁ እልል(፪)
ለዓለመ ዓለም አማኑኤል እገዛልሃለሁ መድኃኔዓለም(፪)

ቀኑ ጨልሞብኝ ዙሪያው ገደል ሆኖ
የችግር አለንቋ ፊቴ ተደቅኖ
ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ
ፈጽሞ አራቅህልኝ የልቤን ትካዜ

አዝ……

አምላኬ ጉልበቴ ኃይሌ መመኪያዬ
ጠላት ማሳፈሪያ የእምነት ጋሻዬ
እንደማትተወንኝ አሁን አውቄአለሁ
ካለኝ ነገር ይልቅ በአንተ ታምኛለሁ

አዝ……

ጥቂቷን አብዝተህ ለምትመግብ ጌታ
የምመልስልህ ባላገን ውለታ
በቀንም ሌሊትም ሁሌም ለሚያበራ
መንክር ለባህርይሕ እጹብ ለአንተ ሥራ

አዝ……

አምላክ ሆይ ምስጋና ለአንተ ይገባሃል
ለምስኪኗ ጎጆ በረከት ሰጥተሃል
ድሃ ነኝ አልልም ሀብቴ አንተ ነህና
ማሰሮዬ ሞልቷል ላይጎድል እንደገና

## <u>ንግስተ ሰማያት</u>

ንግስተ ሰያት ወምድር ማርያም ድንግል(፪)
ተፈጸመ(፫) ማህሌተ ጽጌ (፪)

## <u>ማህደረ  መለኮት</u>

ማህደረ መለኮት(፪)
ማርያም እመ ብዙሃን(፪)